# በደልን መላመድ ባርነት ነው !

አሥራደው (ከፈረንሳይ)



ሕሊና አገር ነው፤ ሕሊና ነፃነት ነው፤ ሕሊና ፍቅር ነው፤  ሕሊና እምነት ነው፤ ሕሊና ማንነት ነው፤ ሕሊና ባህል ነው፤ ሕሊና ቋንቋ ነው፤ ሕሊና ሃቅ ነው፤ ሕሊና ለወገን ዘብ በመቆም: ለአገር፤ ለሕዝብና ለራስ ክብር ሲሉ በአንድ ላይ አብሮ በመነሳት ነፃ ሕዝብ መሆን ነው!!! .................. ታዲያ እነዚህን ሁሉ የፈረንጅ አገር ቂጣ አይተካቸውም ፤ (ሕሊናውን ለታደሉ)::  ከጽሁፉ ውስጥ የተቀነጨበ::

ኢትዮጵያ በጣም ለም አገር ናት፤ ካድሬና  ሙሰኞች (ነቀዞች) እየዘራች  ሌብነት ታመርታለች!!!!

***<u>መንደርደርያ</u>***

1. " un patrie sans justice est un prison"

Georges Clemenceau

" ፍትህ የሌለበት አገር እንደ እስር ቤት ይቆጠራል "

ጆርጅ  ክሊመንሶ

2. "Il n'est point de bonheur sans liberté, ni de liberté sans courage"

Périclès,  homme politique grec  (429- 495 JC)

" መደሰት (ደስታ) ያለ ነፃነት እንደማይኖር ሁሉ ፤  ነፃነትም ያለ ድፍረት (ያለ ጥንካሬ) አይኖርም "

ፔሪክሌስ:  ፖለቲከኛ የግሪክ ሰው  (429 - 495 ከክርስቶት ልደት በፊት) የኖረ

3. "Le courage c'est de chercher la vérité et de la dire".

Jean Jaurès  " ዣን ዡሬስ "

" ድፍረት( ጥንካሬ)  ዕውነትን መፈለግና እሷኑ (ሃቁን) መናገር ነው "

4. " La liberté d'expression c'est faire couler de l'encre, pas faire couler du sang"

d'un inconnu

" ሃሳብን የመግለጽ ነፃነት ቀለምን እንዲፈስ ማድረግ እንጂ፤ የሰው ልጆችን ደም ማፍሰስ አይደለም "

ካልታወቀ

5. " Ne craignez jamais de vous faire des ennemis; si vous n'en avez pas, c'est que vous n'avez rien fait."

Georges Clemenceau

" ጠላት አፈራን ብላችሁ በጭራሽ አትፍሩ (አትጨነቁ)፤ ጠላት ከሌላችሁማ፤ ምንም የረባ ሥራ አልሠራችሁም ማለት ነው!! "

ጆርጅ ክሊመንሶ

6. " Le problème de notre temps n’est pas la bombe atomique, mais le cœur de l’homme."

Albert Einstein

" የዘመናችን ትልቁ ችግር የአቶሚክ ቦንብ ሳይሆን፤ የሰው ልጆች ጨካኝ ልብ ነው " ።

አልበርት አነስታይን

7. « A l'instant où l'esclave décide qu'il ne sera plus esclave, ses chaînes tombent. »

Mahatma Gandhi

" ባርያ፤ ባርያ ላለመሆን በወሰነበት ቅጽበት፤ የባርነት ሰንሰለቱ ይበጠሳል"

መሃተማ ጋንዲ

***<u>መግቢያ</u>*** :

የማሰብ ነፃነት ማጣት: ባርያነት ነው፤ ያሰቡትን አለመናገር: ባርያነት ነው፤ ያሰቡትን አለመጻፍ: ባርያነት ነው፤ ፍትህ ማጣት: ባርያነት ነው፤ ከገዛ አገሩ መሰደድ: ባርያነት ነው፤ ተማሪው "መሬት ለአራሹ" ብሎ በደሙ የዋጀውን የመሬት ባለቤትነት መብት: ከገበሬው ነጥቆ በማፈናቀል: ለድንበር ዘለል ከበርቴ መቸብቸብ፤ የባርያነት ቀንበርን መልሶ መጫን ነው፤ ሠራተኛውን በዓለም አቀፍ ዘራፊ ኢንዱስትሪዎች፤ በገዛ አገሩ ጉልበቱን ማስበዝበዝ: ባርያነትን ማስፈን ነው፤ ምሁራንን በአገራቸው ጉዳይ ተሳትፎ እንዳይኖራቸው በየምክንያቱ ማግለል: ባርነትን እንዲነግሥ ማድረግ ነው፤ ወጣቱን ለሥራ አጥነትና ለስደት መዳረግ አገርን መግደል ነው፤ ዝምታ ባርነትን አሜን ብሎ መቀበል ነው፤ አድር ባይነት: ባርያ መሆን ነው፤ ሕዝብን በገዛ አገሩ የበይ ተመልካች እንዲሆን ማድረግ: የባርነት ሥርአትን ማስፈን ነው፤............ወዘተ ።

በተለይ ከአያት፤ ከቅድም አያቶቹ ነፃነትን የወረሰ ትውልድ: ባርነትን መላመድ ከጀመረ: ሰብዕና ይዋረዳል፤ ዕምነት ይጠፋል፤ ሃብት ይዘረፋል፤ ትውልድ ይበከላል፤ ፍቅር ይጠፋል፤ አንድነት ይናዳል፤ በየቤቱ የበረዶ ግግር ሆኖ በፍርሃት ከመንቀጥቀጥ፤ በተናጠል እየተወራጩ ተነጥሎ ከመመታት፤ በየጎሳው እንደረጋ ውሃ ተከትሮ (እያቆሩ) ከመሽተት፤ በአንድላይ ወጥቶ የነፃነት ፀሐይን መሞቅ፤ በአንድላይ እንደ ዓባይ ውሃ ሞልቶ ገንፍሎ በመፍሰስ፤ ግሳንድሱን ጠራርጎ: ንጹህ የቡራኬ ውሃ በአንድነት አብሮ በመጠጣት፤ የነፃነት ሕብስት አብሮ መቋደስና አዲስ ተስፋን መፈንጠቅ!!
ያ ካልሆነ ባርነት ይነግሣል፤ ሰብዕና ይገሰሳል፤ አገር ይሞታል፤ በወቅቱ በአገራችን ኢትዮጵያ እየሆነ ያለው ይኸው ነው።

ባርያ ቆዳው ጠቆር፤ ጠጉሩ ከርደድ፤ አፍንጫው ጠፍጠፍ፤ ዓይኑ ደፍረስ፤ ሰውነቱ ደንደን፤ ......... ያለ ነው፤ ብሎ የሚያስብ ካለ ተሳስቷል። ነፃነት በሌለበት አገር: ቆንጆዋ ውብ ኮረዳ፤ መልከመልካሙ ጎረምሳ፤ ለግላጋው ወጣት፤ እድሜ ጠገቡ አዛውንት፤ የተማረ፤ ያልተማረ፤ እናት አባት፤ ወንድም እህት፤ እኔም፤ አንተም፤ አንቺም፤ እሱም፤ ................ ገና በማህጸን ውስጥ ያለ ሕፃን እንኳን ሳይቀር፤ ሁላችንም ባርያዎች ነን።

ከዘመናዊ ባርያነት ደግሞ: እንዲያውም የጥንቱ ባርያነት ሳይሻል አይቀርም፤ ( ምንም እንኳን ከዝንጀሮ ቆንጆ ምን ይመራርጡ ቢሆንም) በጥንት ጊዜ ባርያ ፈንጋዩ (የባርያው ባለቤት): ባርያው ሰውነቱ ደንደን ብሎ: ደህና ዋጋ እንዲያወጣለት: ደህና አድርጎ ይመግበው እንደነበር፤ እንዳውም ሊሸጠው ወደ ገበያ ይዞት በሚወጣበት ዕለት: ሰውነቱ እንዲያብለጨልጭ በሞራ በደንብ አድርጎ በማሸት ይንከባከበው እንደ ነበር ታሪክ ይዘክራል።

ዛሬ ወያኔ በኢትዮጵያ ያሰፈነው ባርነት ደግሞ: አመድ እያቦነነ አመድ የሚያለብስ ባርነት ሲሆን፤ አብሮነታችን ስለሚያስፈራው፤ ልዩነቶቻችንን በማራገብ: የዘረኝነት እሳት በኢትዮጵያ አንድዶ እግሩን አንፈራጦ ፍሙን ሲሞቅ ይኸው 25 ዓመታት ሊሞላው ነው። ወያኔ የሸንበቆ ከዘራ ተደግፎ የቆመ አፅም እንኳን ስለሚያስፈራው፤ ተሸብሮ በማሸበር: በጅምላ ማሰር፤ በጠራራ ፀሐይ የኢትዮጵያ ተማሪዎችን መረሸን፤ በኑሮ ውድነት ዜጎችን ማስራብ፤ በስርቆትና በንቅዘት አገር ማራቆት፤ ኢትዮጵያዊነትን እየቦረቦረ ዘረኝነትና ጎጠኝነትን ተክሎ እየኮተኮተ ውሃ ማጠጣት የሌት ተቀን ሥራው በመሆኑ የዜጎች ረሃብና ችግር ፤ መከራና ስቃይ፤ ለሱ ትርፍ እስካስገኘለት ድረስ ደንታ የለውም ።

**<u>የባርነት አይነቶች፤</u>**

- የአካል ባርነት

- የአይምሮ ባርነት

- የምቾት (የቅንጦት) ባርነት፤

- በውጪ አገር በስደት ያለው፤ እራሴን ጨምሮ (ዲያስፖራ ተብሎ የሚጠራው ባርነት)

- የወያኔ ባርነት፤ ሲሆኑ፤

ወያኔ ባርያ ያደረጋቸው፤ (ዓይነታቸው ብዙ ነው)፤ እነሱም:

* **የስልጣን ባርያዎች፤** ከካድሬዎች ጀምሮ በጦር ሃይሉ፤ በፖሊስ፤ በሲቪል ሥራ በስልጣን ላይ ያሉ የወያኔ አገልጋዮች፤
* **የጎሳ ባሪያዎች፤** ለወያኔ ባርያ የሆኑ የትግራይ፤ የአማራ፤ የኦሮሞ፤ የሲዳማ፤ የሃዲያ፤ የአደሬ፤ የወላይታ: የጉራጌ፤ የሱማሌ............ ወዘተ ወግኖቻችን ፤

* **አዲስ ደጅ ጠኚ ባርያዎች፤** ወያኔን ጧት ማታ ደጅ በመጥናት ለሚቀጥለው ዝርፊያ የተዘጋጁ፤ ሕሊና ቢስ ሆዳሞች

* የግድ 5ለ1 በመጠርነፍ ባርያ የተደረጉ ምስኪን ዜጎች ወገኖቻችን................ወዘተ.

**የምሁሩ ባርያነት፤**

ምሁር ተብለው: በንዋይ ፍቅር የታወሩ፤ ድሃ ወገናቸውን በመካድ፤ የወያኔ ባርያነትን የመረጡ፤ (ከተለያዩ ጎሳዎች)፤ ያሉ ሲሆን፤ ከተራው ገበሬና ሠራተኛ አፍ እየተነጠቀ በተሰበሰበ ግብር ተምረው ፤ ሳይማር ያስተማራቸውን ሕዝብ ውለታ በመዘንጋት፤ ከራሳቸው አልፈው ሌላውን ሕዝብ በማስተማርና በማደራጀት፤ ለመብቱና ለነፃነቱ በአንድነት እንዲቆም በማድረግ፤ ለድል እንዲበቃ በማድረግ ፈንታ፤ እራሳቸው ባርነትን አሜን ብለው በመቀበል: ባርያ መሆንን የመረጡ። የምሁሩ ለሆዱ ሲል ባርያ መሆን፤ እጅግ አሳዛኝ ከመሆኑም በላይ፤ አስከፊና አገር ገዳይ ነው።

**የሰፊው ሕዝብ ባርያነት፤**

ይህ ክፍል ወያኔ በጫነበት የባርነት በትር: ዘወትር እየተቀጠቀጠ፤ ለራሱም ሆነ ለልጆቹ ዋስትና በማጣት፤ የዕለት ተዕለት ጉርሱን ለማግኘት ሲባዝን የሚውል ሲሆን፤ የኑሮ ክብደት አጉብጦት ዛሬን ከመኖር ባሻገር: ነገን ለመኖሩ ዋስትና ያጣ ነው። በተማረው ወገኑ ላይ ከፍተኛ ዕምነት ያለውና የነበረው ሲሆን፤ የተማሩ ልጆቹ: ከባርነት፤ ከድህነት፤ ከችግርና ከመከራ ነፃ ያወጡኛል እያለ ሲጠብቅ፤ ብሎም ሲናፈቅ: እንዳልነበር፤ ባልጠበቀው መንገድ: የባርነት ጉድጓድ ሲምሱለት በማየቱ፤ ግራ ገብቶትና ተስፋ ቆርጦ: ዓይኖቹን ወደ ፈጣሪው እያማተረ፤ እጆቹን ዘርግቶ ሻል ያለ ቀን እንዲያመጣለት ፈጣሪውን መማጠን ይዟል።

**በውጪ አገር በስደት ያለነው (የዲያስፖራው) ባርያነት፤**

ምንም እንኳን በፈረንጅ አገር ሥርተን በምናገኘው ንዋይ፤ ሆዳችንን እንዳይርበው: በቂጣ ብንደልለውም፤ የሕሊና ረሃብተኝነታችንን: በምንም ነገር ልንደልለው አንችልም። ጧት፤ ማታ፤ ስንሄድ፤ ስንተኛ፤ብቻችንን፤ ከሰው ጋር ስንሆን፤ ያሳብቅብናል፤ ሠላም እየነሳ ያስጨንቀናል፤ (ሕሊናውን ከታደልን ማለቴ ነው)።

ሕሊና አገር ነው፤ ሕሊና ነፃነት ነው፤ ሕሊና ፍቅር ነው፤  ሕሊና እምነት ነው፤ ሕሊና ማንነት ነው፤ ሕሊና ባህል ነው፤ ሕሊና ቋንቋ ነው፤ ሕሊና ሃቅ ነው፤ ሕሊና ለወገን ዘብ በመቆም ለአገር፤ ለሕዝብና ለራስ ክብር ሲሉ በአንድ ላይ አብሮ በመነሳት ነፃ ሕዝብ መሆን ነው!!! .................. ታዲያ እነዚህን ሁሉ የፈረንጅ አገር ቂጣ አይተካቸውም።

እጅግ የሚያሳስበው፤ ለኛም ለልጆቻችንም የማትሆን ኢትዮጵያ፤ በዘር ሃረግ ስትጎነጎን፤ በጎሳ መጥረቢያ ስትሸነሸን፤ በድንበር ዘለል ከበርቴዎች ስትቦጠቦጥ፤ ማዕድናችን ሲዛቅ፤ ደኖቻችን ሲጨፈጨፉ፤ መሬታችን ሲቸበቸብ፤ በየአቅጣጫው የአገራችን ድንበር ሲሸራረፍ፤ ኢትዮጵያዊነት እየተገዘገዘ ለጥፋት ሲቃረብ፤ ጎሰኝነት ሲያብብ፤ እያየን እንዳላየ በዝምታ ማለፋችን ሲሆን፤ በፈረንጅ አገር ባርነት ላይ የምቾት ባርያነትና፤ የአድር ባይ ባርያነት ጨምረንበት፤ ድርብርብ ባርያዎች ሆነናል።

**<u>ማሳረጊያ</u>**

ባርያ ፈንጋይ: ለባርያዎቹ ነፃነት የሰጠበት ጊዜ የለም፤ ባርያዎች በተናጠል ሳይሆን፤ በአንድላይ፤ እደግመዋለሁ: በአንድላይ ሆነው በማመጽ ብዙ ጊዜ ነፃነታቸውን ማግኘት እንደቻሉ ግን ታሪክ ይነግረናል፤  የአያትና የቅድም አያቶቻችን ለወራሪ ሃይል የአልበገር ባይነት ገድልም የሚያወሳን ይኸንኑ ነው ።

ምንም አይነት ዕውቀትና ችሎታ ኖሮን ብንሠራ: የምናበለጽገውና የምንገነባው የሰው አገር እንጂ የገዛ አገራችንን አይደለም።

ታዲያ ባርያ ፈንጋዩ ወያኔ ነፃነታችንን እንዲሰጠን የምንለምነው እስከመቼ ነው?!

ዛሬ ወያኔ ተክሎ እየኮተኮተ ውሃ የሚያጠጣው፤ የዘረኝነት ቁልቋል ሲያድግ፤ ነገ ሁላችንንም እየወጋ ማድማቱ አይቀሬ ነው፤ በዛሬ ዝምታ ነገ መድማት፤ ወይስ ዛሬ በአንድነት በመነሳት ለነገ ነፃነት መብቃት?!

እስከመቼ በየመንደሩ ትንንሽ ጉልቻዎች ሆነን ፤ ወያኔ የባርነት ድስቱን ጥዶብን እያንተከተከ በእሳት ይለብልበን ?!

ፈረንሳዮች "Aide toi le ciel t'aidera "  ይላሉ "እራስህን እርዳ፤ ከዛ ፈጣሪም ይረዳሃል" ማለት ነው፤

እጃችንን አጣምረን የእኛን ሥራ ፈጣሪ እንዲሠራልን መለመኑን አቁመን፤ የኛን ድርሻ ተግተን በመሥራት

ወደ ነፃነት ምድራችን ኢትዮጵያ በህብረት የምንተመው መቼ ነው ?

ሁላችንም ባርያዎች ሆነናል! ታዲያ መቼ ነው ሁላችንም ነፃ ወ'ተን አገራችንን የምንገነባው ?!

እስቲ ከስደት ባርነትና ከወያኔ ባርነት ነፃ ለመውጣት የወሰንን ስንቶች ነን ? መቼ ?  እንዴት ? ከማንጋር ?

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !

እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ይባርክ !!